# ለጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም (AMEP) ማሻሻያ የተሰበሰበ ግላዊ መረጃ

ለኢሚግሬሽንና ዜግነት መምሪያ (የመምሪያ) ጉዳይ ሲባል የርስዎ ግላዊ መረጃ በጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም (AMEP) አገልግሎት አቅራቢዎች በኩል እንዲሰበሰብ ተጠይቀዋል። ለመረጃ አሰባሰብ ስልጣን በማይግሬሽን አንቀጽ ህግ (*Migration Act 1958*) ዓ.ም በክፍል 2 ስር ባለው መሰረት ይሆናል።.

የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ የመንግሥት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ጉዳይ ለማካሄድ ምናልባት ለሌላ ወኪሎች ወይም ድርጅቶች ሊሰጥ እንደሚችል ነው። በዚህ ፕሮግራምና አገልግሎት የሚካተት:

- ህጻን እንክብካቤ ማእከላት፤ ስለዚህ የAMEP ፕሮግራም የሚፈቀድላቸው ደንበኞች የህጻን እንክብካቤ መስጫ ይቀርብላቸዋል
- በሥራና ሰራተኛ እንዲሁም በስልጠና ፕሮግራም በAMEP ሰፈራ ቋንቋ ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑ ቀጣሪዎች
- በቅርቡ ለመጡ ስደተኞች የሰፈራ አገልግሎትን ለመስጠት መምሪያው ለአገልግሎት አቅራቢዎች ያነጋግራል
- የመንግሥት መምሪያ ቢሮዎች፤ በዚህ የሚካተት:
    - ሴንተርሊንክ (Centrelink); የመንግሥት አበሎችንና ጥቅሞችን ያስተዳድራል;
    - የሥራና የሥራ ቦታ ግንኙነት መምሪያ (DEEWR); እንዲሁም
    - ለሥራና የሥራ ቦታ ግንኙነት መምሪያን (DEEWR) ወክለው አገልግሎት እንዲያቀርቡ ለአገልግሎት አቅራቢዎች ማነጋገር ይህም ሥራ አገልግሎት አውስትራሊያ (Job Services Australia) እና የአካለ ጉዳተኛ የሥራና ሰራተኛ አገልግሎትን ያካትታል
- ለማጣራት ወይም በድንገተኛ ችግር ጊዜ እንዲረዱ የፌደራል፣ የአስተዳደር ግዛትና የተሪቶሪ ፖሊስ መምሪያዎች ናቸው።

በተጨማሪም በመረጃ ማቅረቢያ ቅጽ 993i የግላዊ መረጃዎን ደህንነት መጠበቅ (Safeguarding your personal information) ላይ ለማን መረጃ እንደሚሰጥ የድርጅቶች ዝርዝር ይሰጣል። ቅጽ 993i በመምሪያው ድረገጽ www.immi.gov.au/allforms/ ላይ ሲገኝ ወይም በማንኛውም መምሪያ ወይም በውጭ አገር የአውስትራሊያ ተልእኮ/ሚሽን ጽህፈት ቤት ይገኛል።.

## የርስዎ መብቶች

አገልግሎት አቅራቢው ወይም መምሪያው በስህተት መረጃ ሰብስቧል ወይም በአግባቡ አልያዘም ብለው ካመኑበት ለሚከተለው መጻፍ ይችላሉ:

The Director
Freedom of Information and Privacy Policy Section
Department of Immigration and Citizenship
PO Box 25
BELCONNEN ACT 2616

ወይም ኢሜል privacy@immi.gov.au

ያቀረቡት ቅሬታ ተመርምሮ ውጤቱ ይነገርዎታል።